# የሰላም መድረኮቻችንን ለማስፋት

**ዮናስ** 04-12-18

አገራችን የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ ብዝኃነትን በማያስተናግዱ ሥርዓቶች ምክንያት ለእርስ በርስ ግጭቶች ስትዳረግ መቆየቷ አይታበልም። በተለያዩ ዘመናት ረዥም ጊዜን የወሰዱ፣ የሰው ሕይወትና ሀብት ያወደሙ ጦርነቶችም ሲስተናገዱ ነበር። ይህ እውነት ለዘመናት ተጫጭኖን ስለነበርም ለድህነት ምንጭ ሆኖብን እንደቆየ አይዘነጋም። በእርስ በርስ ግጭቶቻችንና በድህነታችን ምክንያትም ለውጭ ጠላቶች ተጋላጭ የሆንንባቸው ወቅቶችም በርካታ ናቸው። በዚህም በተለያዩ ዘመናት አገራችን በርካታ የውጭ ወረራዎችን ለመጋፈጥ ስትገደድ ቆይታለች።

አገራችን ባስተናገደቻቸው የማያባሩ የእርስ በርስ ጦርነቶችና ብዝኃነትን በማያስተናግዱ ሥርዓቶች ምክንያት ድህነትና ኋላቀርነት እየተባባሱ ከነበረችበት የሥልጣኔ ማማ ወርዳ የቁልቁለት ጉዞ መጓዟም በታሪክ ተጽፎ ይገኛል። ይህ የቁልቁለት ጉዞ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሶ አገራችንን ለብተና አደጋ አጋልጧት እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። የዚያ ያለፈ አስከፊ ዘመን የዞረ ድምር አሁንም ድረስ ብልጭ፣ ድርግም እያለ መቀጠሉም ሊሸሸግ የሚችል አይደለም።

መላው የአገራችን ሕዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት ትግል ግን የቁልቁለት ጉዞውን መግታት ብቻ ሳይሆን፣ አዲስ የተስፋ ብርሃንም መታየት መጀመሩም የሚታወቅ ነው። አገራችንን ወደ ቀደመው ክብሯና ዝናዋ ለመመለስ ያስቻለ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ተዘርግቷል።ያም ሆኖ ግን ይህ ሥርአት ለምክንያታዊነት ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ሳለ ምክንያታዊ ባልሆኑ አግባቦች ከፍ ያለ ነቀፌታና አንዳንዴም ኃይል የተቀላቀለበት ተቃውሞ እየገጠመው መምጣቱ ማንንም ከሰመመን የሚያባንን ወቅታዊ ፈተና ነው። ይህ ብቻ አይደለም ህገ መንግስታዊ ሥርአቱን በህግ አግባብ ማስከበር ያልተቻለበትም ሁኔታ ተፈጥሯል። ስለሆነም በመደበኛው ህግ ማስከበር ያልተቻለውን ቀውስ ሥርአቱን መነሻ ባደረገ አዋጅ ለማስከበር መሻት ህገ መንግስታዊም ምክንያታዊም ይሆናል።ይህ መፍትሄ በእርግጥ ጊዚያዊ ነው። ይህም ማለት ሃገሪቱ ዘላቂ ለሆኑ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ልትረባረብ የሚገባት ሰዓት ላይ ነች ማለት ይሆናል።ከቀው ሱ መንስኤዎች አኳያ ለዘላቂ ሰላም ቀዳሚው አጀንዳ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን የሚያጠናክሩ የሰላም ኮንፈረንሶች መሆኑ ተገቢነቱ ባያጠያይቅም እነዚህን መድረኮች ማስፋት ግን ቁልፍ የመንግስትና የሰላሙ ባለቤትም ተጠቃሚም የሆነው ህዝብ ሊሆን ይገባል።

በመሰረቱ የሀገሪቱን ሰላምና ልማት ለማስቀጠል ሕዝቡ የአብሮነትና የመቻቻል የባህል እሴቶችን ሊጠበቅና

ሊንከባከብ የሚገባው መሆኑ አያከራክርም። ህዝብ በሰላም አብሮ የመኖር ወርቃማ እሴቶቻችን የሚያደበዝዝ ግጭት እንዳይከሰት ግንባር ቀደም አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ከተገባ መጀመሪያ የርስ በርስ ግንኙነቶችን ማጠናከርና ለዚህ የሚረዱ መድረኮችን ማስፋት ያስፈልጋል።እነዚህ መድረኮች የግጭቶች ሰለባ በነበሩ አካባቢዎች ላይ ብቻ ተወስነው ሊቀሩ አልያም ትኩረት ሊያደርጉ አይገባም።

የኮንፍረንሶቹ አላማ በህዝቡ መካከል ለዘመናት የዘለቀውን አብሮ የመኖርና የመቻቻል የባህል እሴቶችን በማጠናከር የተጀመረው የህዳሴ ጉዞ እንዲጠናከር ማስቻል እስከሆነ ድረስ በመላው ሃገሪቱ የሚገኙ ክልሎች ዞኖች ወረዳዎች ቀበሌዎች መንደሮችና የከተማ አስተዳደሮችም አጀንዳ ሊሆን ይገባዋል። በማናቸውም ሁኔታ ህዝቡ አፍራሽ ሃይሎችን ነቅቶ በመጠበቅ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር ሊያረጋግጥ የሚችለው በዚህ አግባብ የጋራ ግንዛቤ ሲኖረው ነው። የሰላም ኮንፍረንሶቹ ሌላኛ ዓላማ በአካባቢው የሚታዩ አላስፈላጊ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ህዝቡ ራሱ መፍታት የሚችልበትን አግባብ ለመቀመር ነው።

በሃይማኖትና በማንነት ሽፋን የህዝቡን ሰላምና አንድነት ለማናጋት የሚጥሩ ሃይሎችን ነቅቶ በመጠበቅ የአካባቢው ልማት እንዲፋጠን የሚያደረገውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል የሚቻለው መላው ህዝብ በተመሳሳይ ቅኝት ላይ እስከተገኘ ድረስ ብቻ ነው።

ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በፖለቲካና መልካም አስተዳዳር ብቻ ሳይሆን፣ በጎሳ ተኮር ፌዴራላዊ ሥርዓቱና በሀብትና ሥልጣን ክፍፍሉ ላይ የሕዝብ ቅሬታ እየተበራከተ እንደመጣ በአሁኑ ወቅት ለሁለተኛ ጊዜ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መንግሥት እስከማወጅ የገፋው ነባራዊ ሁኔታ ያስገነዝባል። ይህ ክስተትም ዳግም የሕዝቡን የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት፣ እንዲሁም የአገሪቱን የለውጥ ጉዞና የታዳጊ ዴሞክራሲ የማበብ ጅምር እንዲጠናከር ዳግም ሁሉን አቀፍ ውይይትና ብሔራዊ መግባባት በእጅጉ አስፈላጊ ሆኗል።

ከዚያም አልፎ አሁን ባለው ተጨባጭ የአገሪቱ ሁኔታ ለዘመናት ተቻችሎና ተከባብሮ ብቻ ሳይሆን፣ በሚያኮራ አንድነት ፀንቶ የኖረው ኢትዮጵያዊነት ባለፉት 27 ዓመታት እየተንሸራተተ ሲመጣ ኖሮ አሁን ላይ ወደ ከፋ የመገፋፋት ጫፍና የጥላቻ ዝንባሌ መውረዱ ገሀድ ሆኗል። ይህ አስከፊና አጥፊ አካሄድም በማኅበራዊ ድረ ገጾች የጥላቻ አስተምህሮዎች እየታጀበ፣ አንድ የትምህርት ገበታ ላይ ያሉ ወጣቶችን በአንድ መንደርና ከተማ ለዘመናት በአብሮነት የኖሩ ዜጎችን በማንነታቸው ወደ ማነጣጠል፣ ማጋጨትና መጠቃቃት ያልተገባ ተርታ እያወረዳቸው ይገኛል። ይህ ሁኔታም እንደ አገር የሕዝብ አብሮነትና አንድነት እየተሸረሸረ ወደ እርስ በርስ ግጭትና ትርምስ የማምራት ዕድል እንዳይገጥመን ቀላል የማይባል ሥጋት እንዳረበበ ነው። ምንም እንኳን ከዚህ በተቃራኒው ፌዴራሊዝሙ አንድነታችን እያጠናከረው መሆኑ ባይካድም።

በሌላ በኩልም ኢትዮጵያዊያን ለሌላው ጎረቤት አገር አርዓያ ሊሆን በሚችል ደረጃ  የአገር ውስጥ ችግራችንን ሁሉ በውይይት መፍታት የምንችል ሆነን ሳናበቃ፣ አሁንም መገፋፋቱን ስለምን ቀጠልንበት? ለሚለው የብዙዎች ጥያቄ መልስ የሚገኘውም ከነዚህ መድረኮች ነው። አሁን ያለውን አገራዊ ሁኔታ ተጠቅመው የግል ፍላጎታቸውን ለማጋበስ የሚራሯጡ ኃይሎች ክስተቱን ወደ ሁከትና ብጥብጥ እንደ ልባቸው መቀየርና ማዳከም የቻሉት በየትኛው ድክመታችን ገብተው ነው? ብሎ ይህ ክስተት እንዳይደገም የሚያስችል መፍትሄ መቀመር የሚቻለውም በነዚህ መድረኮች  ነው።

በእርግጥ ለረዥም ዘመናት በተፈጥሮ ሀብታችን እንድንለማ የማይፈልጉት እንደ ግብፅ ያሉ (ይኼ ነገር ኤርትራንና አንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችንም ይጨምራል) አገሮች በግልጽም በሥውርም ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ተሠልፈው እኛን ለማዳከም መሥራታቸው የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ የቆየ ነው። ይሁንና የእነዚህን ኃይሎች አስተሳሳብ የሚሸከምና ወደ ነውጥና አመፅ፣ በተለይም የፖለቲካ ፍላጎትን በኃይል ለማሳካት እርስ በርስ ወደ መባላት የሚያተኩር ወጣት ኃይልና ዜጋ እንዲበራከት ያደረጉ ሃይሎችን ለመለየትና በቀጣይ ሴራቸውን ማክሸፍ የሚቻልባቸው አግባቦችን መተለምም የሚቻለው እነዚን መድረኮች አስፍተን ስንጠቀምባቸው ነው።

በመቼውም ጊዜ ቢሆን በተለይ አንዳንድ የውጭ ኃይሎቹ ለእኛ አገራዊ ተጠቃሚነት ብቻ አስበው የሚሠሩልን ተግባር ፲ቢበዛ ለጋራ ተጠቃሚነት ካልሆነ በስተቀር የለም። የአገር ውስጥ የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮቻችንም ይሁኑ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች መቼም ቢሆን በውጭ ኃይሎች ድጋፍ ብቻ ሊፈቱ አይችሉም። አንዳንድ አጋር መሰል ኃይሎች ደግሞ ዓላማቸው ወደ ቀደመው የትርምስ መንገድ ተመልሰን እርስ በርስ እንድንተላለቅና ደካማና የተበታተነች ኢትዮጵያን ከመሻት የመነጨ እንደሆነ ተገንዝበን፣ በሆደ ሰፊነትና በመተማመን በአገራችን ጉዳይ ላይ ሁሉም ወገኖች መመካከር እንዳለብን መዘንጋት የለብንም።

አንድ የማይካድ እውነት ባለፉት ሦስት ዓመታት በአገራችን ግልጽ ሊባል የሚችል የዴሞክራሲና የፖለቲካ ተሳትፎ ጥያቄ ተንፀባርቋል። የሕዝቡን ትክክለኛ ጥያቄዎች ጠልፈው ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ ኃይሎች ችግሩ ገጽታውን ቀይሮ እንዲባባስ ማድረጋቸው ግን የማይበጅንና መወገዝ ያለበት ነው።

ያም ሆኖ ግን እንደ ዜጋ ኢትዮጵያዊያን በአሁኑ ወቅታዊ ከአገራችን ነበራዊ ሁኔታ ረገድ ምን እናድርግ? ምንስ ይጠበቅብናል? ብሎ በሆደ ሰፊነት መነጋጋር ለነገ የሚባል ተግባር አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥንትም ሆነ ዛሬ ክፉውንም፣ ደጉንም በአንድነት የሚያሳልፉ፣ ተዋልደውና ተዋህደው

የኖሩ ናቸው። ምንም እንኳን ጉዳዩ በየጊዜው አገዛዞችም ይባሉ የውጭ ኃይሎች ዘርን ከዘር ለመነጣጠል የተጠቀሙበት መሆኑ ባይካድም፣ በጭቆና ውስጥ እንኳን ሕዝቡ ፈሪኃ አምላክ ያለውና አገሩንና አንድነቱን የሚወድ እንደሆነ በተደጋጋሚ አሳይቷል። ከዚህ በኋላም ያለፈው አልፏል ብለን በአንድነትና በጠንካራ ኅብረ ብሔራዊነት ለመቆም መላው ሕዝብ፣ በተለይም ፖለቲከኞችና የሃይማኖት መሪዎች በትኩረት ሊሠሩበት ይገባል።

እዚህ ላይ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ቢሆንም እስካሁን በትኩረት የሠራበት መስክ ባይሆንም፣ በሕገ መንግሥቱም የተጣለበትን አንድነትን የማጠናከር ግዴታ በወጉ ተገንዝቦ ሊረባረብ ይገባዋል። ይህን ሀቅ በተገቢው ለማስታወስ  የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ሕገ መንግሥት አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 2 መጥቀስ ያስፈልጋል። <<መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር  ግዴታ አለበት?» ይላል።

ከዚህ መሠረታዊ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ አንፃርም ሆነ ለዘመናት አብሮን ከኖረው ሕዝባዊ ኅብረት አንፃር ያለንበትን ሁኔታ ስንፈትሽ ድክመት እንደሚታይ ብዙዎችን እያግባባ ነው። በአገሪቱ በተለይ የሕዝቦች አንድነትና ወንድማማችነት ያለበትን ደረጃ በጥሞና ለፈተሸው፣ ባለፉት 25 ዓመታት ላላቶ፣ ላልቶ ወደ ውድቀት ጫፍ እያደረሰን እንደመጣ አሁን ባለው ተጨባጭ የብሔር መገፋፋትና አንዱ ሌላውን የማሳዳድ ድርጊት በግልጽ እንደታየ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው።

ሕገ መንግሥታዊ ግዴታ የተጣለበት መንግሥትም ቢሆን ለብሔር ብሔረሰቦች ማንነት፣ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ በእኩልነት መከበርና መስፋፋት ረገድ የሰጠውን ትኩረት ያህል ለሕዝቦች አብሮነት፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ወንድማማችነት መስፈን ያከናወነው ተግባር አርኪ እንዳልነበር ራሱ ሥርዓቱ ግለ ሒስ ማድረጉ ብቻ በቂ አይደለም። ይልቁንም በአፋጣኝ በጉዳዩ ዙሪያ ሕዝቡን፣ ምሁራኑንና ፖለቲከኞችን አወያይቶ፣ የራሱንም አደረጃጀት ወደ ውህደትና ጠንካራ ኅብረት ቀይሮ ሕዝቦች በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊነት አብሮነት ማንነታቸውን አስጠብቀው፣ ግን አገራዊ ማንነታቸውን እንዲያጠናክሩ በድፍረት ሊታገል ይገባል። የኅብረትና የአንድነት ችቦውም በግልጽ ስትራቴጂ እየተመራ ሊለኮስ ግድ ይለዋል።

ከዚህ አንፃር መንግሥት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅም ሆነ በመደበኛው የሕግ የበላይነት ሥርዓት ዕውን መሆን የተጣለበት ኃላፊነት በንቃትና በትጋት መወጣት አለበት። በሌላ በኩል በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡ የዜጎች የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች በማክበርና በማስከበር ትውልዳዊ ኃላፊነቱ ሊወጣ ግድ ይለዋል። በተለይ በአገሪቱ የተከሰተውን የፖለቲካ በሽታና የዴሞክራሲያዊ ምኅዳር ውድቀት ካረበበበት ያለመግባባት ጨለማ አውጥቶ

የአገሪቱን ሕዝቦች ሳይነጣጥል አሳታፊ በሆነ መንገድ ለማስቀጠል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሁሉ መክሮ ዘላቂ መፍትሔ ማስቀመጥና ለዚያም መረባረብ ይኖርበታል፣ ግዴታም አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚታወቅባቸው ዋነኛ መለያዎቹ መካከል ለአገሩ ያለው ጥልቅ ፍቅር አንደኛው ነው። ይህ የአገር ፍቅር ስሜት ራስን በፈቃደኝነት ለመስዋዕትነት ከማቅረብ ጀምሮ፣ በልዩ ልዩ አበርክቶዎች እየተገለጸ ዘመናትን መሻገር ተችሏል። ይህ ኩሩና ጨዋ ሕዝብ በአገሩ ጉዳይ ከማንም ጋር ተደራድሮ አያውቅም። አገሩን በክፉ የሚያዩትን ጭምር ሲፋለም ኖሯል። ለዘመናት ከወራሪዎችና ከተስፋፊዎች ጋር እየተፋለመ እናት አገሩን ሲጠብቅ የኖረው፣ ከአገሩ በላይ ምንም የሚያስቀድመው ባለመኖሩ ነው። ይህ አስተዋይ ሕዝብ በፊትም ሆነ አሁን አገሩን የሚያየው እንደ ዓይን ብሌኑ ስለሆነ፣ አገሩን የሚነኩበትንም ሆነ ለአደጋ የሚያጋልጧትን በፍፁም አይቀበልም። ይህንን ታሪካዊና አንፀባራቂ የአገር ፍቅር ስሜት በተለያዩ ጊዜያት ለማጥፋት የተደረጉ ሙከራዎችም አልተሳኩም። ሕዝባችን በእርስ በርስ መስተጋብሩም ሆነ ከባዕዳን ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ቅድሚያ የሚሰጠው ለአገሩ ብቻ ነው። ይህንን ሀቅ መረዳት ያቃታቸው ወይም የማይፈልጉ ግን ከፍላጎቱ በተቃራኒ ስህተት እየፈጸሙ ነው። ሕዝቡ በአገሩ ላይ ከሚቆምሩ የሥልጣን ጥመኞችም ሆነ የጠላት ተላላኪዎች ጋር በፍፁም የማይግባበትን እድል ለመፍጠር መድረኮቹ ወሳኝ ይሆናሉ።